# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር

## ከተሽከርካሪ የሚወጣ በካይ ጋዝ ልቀት ቁጥጥር መመሪያ

## ቁጥር 1051/2017

# Federal Democratic Republic of Ethiopia

## Ministry of Transport and Logistics

## Directive on Emission Control of Pollutants from Vehicle No.1051/2025

መጋቢት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መመሪያ ቁጥር1051/2017

## ከተሽከርካሪ የሚወጣ በካይ ጋዝ ልቀት ቁጥጥር መመሪያ

ኢትዮጵያ የፈረመችበት የፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት የዓለም የሙቀት መጠን ከኢንዱስትሪዎች ከ2°C በታች እንዲሆንና እና እንደ አጠቃላይ የሙቀት መጠኑ ከ1.5°C እንዳይበልጥ ጥረቶችን ማድረግ ሲሆን ከትራንስፖርት ዘርፉ 20% የልቀት ድርሻ ትልቁን መጠን የሚይዘው የመንገድ ትራንስፖርት (ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ ልቀት) በመሆኑ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን ሁሉም ሰዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብትን ከዚህ የዓለም አቀፍ ጥረት ጋር በማስማማት ተሽከርካሪ ለአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርገውን አስተዋፅዖ መቆጣጠር በማስፈለጉ፤

በሀገራችን በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኘውን ኢኮኖሚ ከአካባቢና ማኅበረሰብ ልማት ደኅንነት ጋር በተስማማ መልኩ በዘላቂነት ለማስቀጠል እና የዜጎች መብት ከማስጠበቅ አንፃር በኢትዮጵያ ከተመዘገቡና በመላ ሀገሪቱ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የሚወጣው የበካይ ጋዝ ልቀት በጤና ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ፣ ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂና በካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቀነስ

## Directive No. 1051/2025

## Directive on Emission Control of Pollutants from Vehicle

Ethiopia, as a signatory to the Paris Agreement on Climate Change, is committed to contributing to global efforts to limit the rise in global temperatures to below 2°C for industrial activities and 1.5°C overall. Road transport, which constitutes 20% of emissions in the transport sector, is a significant contributor to greenhouse gas emissions. In alignment with these international objectives and in recognition of the right of every individual to live in a clean and healthy environment as enshrined in Article 44, Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, there is an urgent need to regulate vehicle emissions.

To support the sustainable growth of Ethiopia's rapidly expanding economy while ensuring environmental protection and social well-being, it is imperative to establish a robust system to mitigate the adverse health impacts of greenhouse gas emissions. This

የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የወጣውን ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቅ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን በመተግበር የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን በመቀነስ የአካባቢና የአየር ብክለትን ለመከላከል እና በካይ ጋዝ ልቀት መቀነሻ ቴክኖሎጂን በተሽከርካሪዎች ላይ በመግጠም የአካባቢ ደኅንነትን በማረጋገጥ ለዜጎች ምቹና ጤናማ አካባቢ ለመፍጠር እንዲያስችል፤

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “ከተሽከርካሪ የሚወጣ በካይ ጋዝ ልቀት ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1051/2017” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

system will target emissions from vehicles registered and operated nationwide, aiming to reduce their contribution to atmospheric pollution.

Whereas, it is essential to implement the Greenhouse Gas Emission Standards for Vehicles, as established by the Ethiopian Standards Institute, to curtail emissions and combat air and environmental pollution and mandate the adoption of greenhouse gas emission reduction technologies in vehicles to promote environmental safety and foster a clean, healthy, and livable environment for all citizens.

The Ministry of Transport and Logistics issued this directive in accordance with Article 12 (2) of Road Transport Proclamation No. 1274/2022.

## Part one

## General Provisions

### 1. Short title

This directive may be cited as **“Directive on Emission Control of Pollutants from Vehicle No. 1051 /2025**.”

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 ነው፤
2) **"አግባብነት ያለው አካል"** ማለት ትራንስፖርትን ለመምራት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ነው፤
3) **"የበካይ ጋዝልቀት መጠን ደረጃ"** ማለት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የጸደቀ ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን መወሰኛ ስታንዳርድ ነው፤
4) **"የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ"** ማለት የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመለካት ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለሚያቀርቡ ድርጅቶች ወይም ለቴክኒክ ምርመራ ተቋማት ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
5) **"የምስክር ወረቀት"** ማለት የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን በሚለካ ድርጅት ወይም የምርመራ ተቋም አማካይነት ተለክቶ በኢትዮጵያ ደረጃዎች

## 2. Definitions

Under this Directive, unless the context requires otherwise:

1) "**Proclamation**" means Road Transport Proclamation No. 1274/2022;
2) "**Appropriate Organ**" refers to the transportation office of a state or city government that is authorized by law to oversee transportation activities;
3) "**Pollutant gas emission level Standard**" means the standard for determining the amount of pollutant gas emitted from vehicles approved by the Ethiopian Standards Institute;
4) **"Competency Assurance License"** means a license issued by the Ministry or the appropriate organ for enterprise that provide technological results to reduce the amount of polluting gas emissions from vehicles or for technical inspection institutions.
5) "**Certificate**" means a proofing paper given to a vehicle that meets the **pollutant** gas emission level standard issued

ኢንስቲትዩት የወጣውን ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን ላሟላ ተሽከርካሪ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን በሚለካ ድርጅት ወይም በምርመራ ተቋም የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

6) “**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤
7) በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች እንደ አግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፤
8) በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሕግ በተደነገገው መሠረት ዓመታዊ ምርመራ እንዲደርጉ በሚጠበቅባቸውና በመላ አገሪቱ ተመዝግበው በሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች፣ በተሽከርካሪ ገጣጣሚዎች፣ አምራቾች እና አስመጪዎች፣ እንዲሁም በተሽከርካሪ ባለንብቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

by the Ethiopian Standards Institute, after the vehicle measured by an inspection entity;

6) "**Person**" means a natural or juridical person;

7) Words and phrases defined under Article 2 of the Proclamation shall apply to this directive as appropriate;
8) Any expression in the masculine gender under this Directive includes the feminine gender.

## 3. <u>Scope of application</u>

This Directive, in accordance with provided law, shall be applicable on vehicles which are required to undergo an annual inspection, registered and operated all over the country, vehicles assemblers, Manufacturers, importers and vehicles owners as well.

## **ክፍል ሁለት**

## **ስለ መስፈርቶች እና ስለ ልዩ ልዩ አካላት ግዴታዎች**

4. **ተሽከርካሪ ማሟላት ስላለበት መስፈርቶች**

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ወይም በሀገር ውስጥ የተገጣጠመ ወይም የተመረተ አዲስ ወይም ያገለገለ ወይም በአገልግሎት ላይ የሚገኝ፣ በነዳጅ የሚሠራ ማንኛውም ተሽከርካሪ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

1) በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የጸደቀውን የበካይ ጋዝ ልቀት ደረጃ አሟልቶ የመገኘት፤

2) በዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ (በሎ) ወይም በድንገተኛ የክትትልና ቁጥጥር ወቅት የተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን አሟልቶ የመገኘት፤

3) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን ያላሟላ ተሽከርካሪ የበካይ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም፤

4) የነዳጅ እና የአየር ማጣሪያ ቴክኖሎጂዎችና ሲስተሞችን ጥቅም ላይ የማዋል፤

## **Part Two**

## **About requirements and obligations of various parties**

4. **The requirements that the vehicle must meet**

Any fuel-user vehicle imported or assembled or manufactured in the country, new or used or in service, must meet the following requirements:

1) It shall met the level of pollutant gas emission standard approved by the Ethiopian Standards Institute;
2) Meeting the standard of pollutant gas emissions during the annual technical inspection or emergency monitoring and control of vehicles;
3) Installing a device reducing the emissions of vehicles that do not meet emissionstandards;
4) Adopt fuel and air purification technologies and systems.

## 5. የተሽከርካሪ ባለንብረት ግዴታዎች

ከተሽከርካሪ የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቀነስ ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለቤት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1) ተሽከርካሪውን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን በሚያስለካበት ወይም በሚያስመረምርበት ወቅት የተሽከርካሪውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር(ሊብሬ) ዋናውን እና ኮፒ ይዞ ለምርመራ ተቋሙ የማቅረብ፤
2) በየዓመቱ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ምርመራ የማድረግና ስታንዳርዱን አሟልቶ የመገኘት፤
3) ተሽከርካሪውን ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ (ቦሎ) በሚያስመረምርበት ወቅት በወጣው የኢትዮጵያ የበካይ ጋዝ ልቀት ደረጃ መሠረት በየዓመቱ የማስመርመርና ደረጃውን ማሟላቱን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት የመያዝ፤
4) የበካይ ጋዝ ልቀት ደረጃን ያላሟሉ ተሽከርካሪዎችን ያለአግባብ ምርመራውን በማሳለፍ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሰጠ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ተቋም ሲያጋጥም ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ጥቆማ የመስጠት፤

## 5. Obligations of the vehicle owner

Any vehicle owner has the following obligations to reduce the amount of pollutant gas emitted from the vehicle:

1) To present the original and a copy of the vehicle title certificate book (Libre) to the inspection institute when measuring or inspecting the vehicle for exhaust gas emissions;
2) Checking the amount of pollutant gas emissions every year and complying with standard;
3) Conduct an annual inspection of vehicles in accordance with the Ethiopian Pollutant Gas Emission Standard, as part of the annual technical inspection (Bolo), and issue a certificate confirming compliance with the standard;
4) To give suggestions to the ministry or the appropriate organ in the case of a vehicle technical inspection facility that has given a certificate of approval by improperly passing the inspection of vehicles that do

5) ሀገሪቱ የምታስገባውን ነዳጅ ከሕጋዊ የነዳጅ ማደያ ቦታ ብቻ በመግዛት የመጠቀም፤
6) ቀጣይነት ያለው የተሽከርካሪ ጥገና የማከናወን፣ ተሽከርካሪው በቴክኒክ ብቁ እና የተሟላ ዕቃ እንዲኖረው የማድረግ፤
7) የተሽከርካሪውን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን ማሟላቱን የሚያረጋግጥ የምርመራ ምስክር ወረቀት ከተሽከርካሪው ጋር ይዞ የመንቀሳቀስ፤
8) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቀነስ በተሽከርካሪው ላይ የሚገጠመው የቴክኖሎጂ መሣሪያ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የወጣውን ደረጃ ያሟላ መሆኑን ከሚኒስቴሩ በሚሰጥ የምስክር ወረቀት የማረጋገጥ፤
9) ተሽከርካሪ የበካይ ጋዝልቀት መጠን ደረጃን ማሟላቱን የሚያረጋግጥ የምርመራ ምስክር ወረቀት የአገልግሎት ዘመኑ ሲያበቃ በየዓመቱ ሲያስመርምር የማሳደስ፤
10) የተሽከርካሪ የበካይ ጋዝ ልቀት ምርመራን በሚኒስቴሩ ወይም ከሚኒስቴሩ የውክልና ሥልጣን በተሰጠው አግባብነት ባለው አካል ወይም በተፈቀደለት የተሽከርካሪ

not meet the emission standards;
5) To use the fuel imported by the country only by purchasing it from a legal gas station;
6) Carrying out continuous vehicle maintenance and making it technically and physically fit;
7) Carrying the vehicle's inspection certificate confirming that the vehicle meets the emissions standards;
8) To ensure that the technological device installed on vehicle to reduce the amount of polluting gas emissions meets the standards issued by the Ethiopian Standards Institute;
9) Renewal of the inspection certificate confirming that the vehicle meets the level of pollutant gas emission at the end of its service period every year.
10) Vehicle emission inspections shall only be conducted by the Ministry, a relevant body authorized through a power of attorney by the Ministry, or an authorized vehicle technical inspection institution.

የቴክኒክ ምርመራ ተቋም ብቻ ምርመራ የማድረግ፤

6. **<u>የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመለካት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች</u>**

የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመለካት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

1) የድርጅቱን ወይም የአመልካቹን ስምና ሙሉ አድራሻ፣ የድርጅቱን የንግድ ስም (ካለ)፣ የሥራ አስኪያጁን ስም የሚገልጽ የማመልከቻ ፎርም መሙላትና ማቅረብ፤

2) የሥራ አስኪያጁ ወይም የባለቤቱ የታደሰ የነዋሪነት እና የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ዋናው እና ኮፒ፤

3) ቢሮ፣ ሁለት እና ከዚያ በላይ ተሽከርካሪዎችን ማስቆም የሚችል ከ40 ሜትር ካሬ የማያንስ የመሥሪያ ቦታ ያለው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ዋናው እና ኮፒ፤ ወይም

6. **<u>The requirements that must be met to obtain a Competency Assurance License for measuring pollutant gas emissions</u>**

Any individual or enterprise that wants to obtain a competency assurance license to measure the amount of pollutant gas emissions must meet the following requirements:

1) Filling and submitting an application form stating the name and full address of the enterprise or the applicant, the business name of the enterprise (if any), and the name of the manager;
2) The original and copy of the renewed residential identity card and national identity card of the manager or owner;
3) An office, the original and a copy of the Title Certificate of House confirming that it has an office space of not less than 40 square meters that can park not less than two vehicles; or

4) If the workplace is rental, the original and copy of the rental

4) የመሥሪያው ቦታ በኪራይ ከሆነ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተረጋገጠ የኪራይ ውል ዋናው እና ኮፒ፤
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው ቢኖርም የቦታው ኪራይ የተፈረመው ከመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም ከሃይማኖት ተቋም ጋር ከሆነ በተቋማቱ ኃላፊ የተፈረመና የአከራዩ እና የተከራዩ ተቋማት ክብ ማኅተም ካረፈበት በቂ ነው፤
6) የሚያቀርበው ወይም የሚያሰራጨው ወይም የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቀነስ የሚገጥመው ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ደረጃ የወጣለት መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፣
7) ጥያቄው የቀረበው በውክልና ከሆነ በሰነዶች መረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ፣ የወካይ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ እና ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ እና የተወካይ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና ኮፒ፣
8) ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ያሟላ ግለሰብ ወይም ድርጅት

agreement certified by the document verification and registration service;
5) Notwithstanding the provisions of sub-article (4) of this Article, if the rent of the place is signed with a public enterprise or a religious institution, it is sufficient if it is signed by the head of the institutions and bears the seal of the lessor and tenant enterprise;
6) A letter confirming that the technology provided, distributed, or utilized to reduce greenhouse gas emissions is certified as meeting the standards of the Ethiopian Standards Institute;
7) If the request is submitted by an agent, the proof of the power of attorney certified by the document verification and registration service and the original and copy of the renewed residential identity card and National Identity Card of the principal and renewed residential identity card or passport of the agent.
8) A qualification authorization for an individual or organization

የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለዉ አካል ይሰጠዋል፡፡

that fulfills the above requirements shall be issued by the Ministry or the relevant authority.

## 7. <u>የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመለካት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ድርጅት ወይም ግለሰብ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመለካት ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1) የበካይ ጋዝ ልቀት መለኪያ መሣሪያውን በየዓመቱ በኢትዮጵያ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት በማረጋገጥ ብቃቱን የሚያረጋግጥ የካሊብሬሽን ምስክር ወረቀት መያዝ፤
2) የተሽከርካሪዎችን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ብቻ የመለካት፤
3) የበካይ ጋዝልቀት መጠን ለተመረመረ ተሽከርካሪ የተቀመጠውን ሀገራዊ ደረጃሲያሟላ የምርመራ ውጤት ሰርተፍኬት የመስጠት፤

## 7. <u>Obligations of an enterprise or an individual who has taken a Competency Assurance License to measure pollutant gas emissions</u>

Any enterprise or individual that has been granted a competency assurance license by the Ministry or the appropriate organ to measure the amount of pollutant gas emissions shall have the following obligations:

1) Having a calibration certificate confirming the efficiency of the pollutant gas emission measurement device by checking it every year at the Ethiopian Metrology Institute;
2) To measure the amount of pollutant gas emission of vehicles only according to the set standards;
3) Issuing a test result certificate when the amount of pollutant gas emission meets the national standard for a tested vehicle;

4) በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ፣ ለሚገጣጠሙ እና ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ አዲስ ወይም ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ደረጃውን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የምርመራ ውጤት ምስክር ወረቀት የመስጠት፤

5) የተመረመሩ ተሽከርካሪዎችን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር(ሊብሬ) ኮፒ እና ሌሎች መረጃዎችን በዓይነትና በብዛት ለይቶና አደራጅቶ በየሦስት ወር ለሚኒስቴሩ ወይም ውክልና ለተሰጠው አግባብነት ያለው አካል ሪፖርት የማድረግ፤

## 8. <u>የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መሣሪያ አቅራቢ፣ አሰራጭ ወይም ገጣሚ ድርጅት ወይም ግለሰብ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች</u>

ማንኛውም የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መሣሪያ አቅራቢ ፣አሰራጭ ወይም ገጣሚ ግለሰብ ወይም ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማውጣት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

4) Issuing a test result certificate confirming that new or used vehicles imported, manufactured and assembled in the country meet the standards;

5) To identify and organize the copy of the title certificate book (Libre) of inspected vehicles and other information by type and quantity and report every three months to the ministry or the appropriate organ that has been delegated.

## 8. <u>Requirements that must be met to obtain a competency assurance license for technology devices aimed at reducing emissions, whether for a provider, distributor, assembler enterprise, or individual</u>

Any technology device aimed at reducing emissions, whether for a provider, distributer or assembler enterprise or individual to obtain a competency assurance license, must meet the requirements under Article 6 of this directive and submit it to the Ministry or the appropriate organ.

## 9. የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መሣሪያ አቅራቢ፣ አሰራጭ ወይም ገጣሚ ድርጅት ወይም ግለሰብ ግዴታዎች

የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችልየቴክኖሎጂ መሣሪያ ለማቅረብ፣ ለማሰራጨት ወይም ለመግጠም የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ወይም ውክልና ከተሰጠው አግባብነት ያለው አካል የወሰደ ማንኛውም ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል:-

1) የድርጅቱን ወይም የአመልካቹን ስምና ሙሉ አድራሻ፣ የድርጅቱን የንግድ ስም (ካለ)፣ የሥራ አስኪያጁን ስም የሚገልጽ የማመልከቻ ፎርም መሙላትና ማቅረብ፤

2) በሚያቀርበው ወይም በሚገጥመው ወይም በሚያሰራጨው ቴክኖሎጂ ላይ በቂ ዕውቀት ያለው እና የሙያ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆኑን የማረጋገጥ፤

3) የሚያቀርበው ወይም የሚያሰራጨው ወይም የሚገጥመው የቴክኖሎጂ መሣሪያ በኢትዮጵያን ደረጃዎች ኢንስቲትዩት በጸደቀውን ደረጃ መሠረት

## 9. Obligations of Technology Device aimed at reducing emissions, whether for a Supplier, Distributer assembler enterprise or Individual Organizations

Any enterprise or individual that obtains a competency assurance license from the Ministry or a delegated appropriate organ to supply, distribute or install a technology device to reduce pollutant gas emissions shall have the following obligations:

1) Filling and submitting an application form stating the name and full address of the enterprise or the applicant, the business name of the enterprise (if any), and the name of the manager;
2) Ensuring that there are experts who have sufficient knowledge and can provide evidence on the technology that is being presented or applied or distributed;
3) To ensure that the technological device that is provided or distributed or installed meets the standards approved by the

ከሚኒስቴሩ መሣሪያው ደረጃውን ያሟላ መሆኑን የማረጋገጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ፤

4) ስለሚያቀርበው ወይም ስለሚገጥመው ወይም ስለሚያሰራጨው የቴክኖሎጂ መሣሪያ አጠቃቀም ማንዋል የማዘጋጀት፤ ሥልጠና የመስጠት፤

5) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መሣሪያ የማስመጣት፣ የመግጠም፣ የመጠገንና ዕድሳት የማድረግ፣ ይህንን ለማከናወን ብቁ ባለሙያዎችን የመቅጠር፣

6) የበካይጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የቴክኖሎጂ መሣሪያ የተገጠመላቸውን ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር(ሊብሬ)፣ ብዛትና ዓይነት በመለየትመረጃዎችን በማደራጀት በኤሌክትሮኒክስ እና በማንዋል በየሦስት ወር ለሚኒስቴሩ ወይም ውክልና ለተሰጠው አግባብነት ያለው አካል የመላክ፤

Ethiopian Standards Institute;

4) To prepare a manual for the usage of technology device that it provides or adapts or distributes and give training;

5) Importing and installing technology devices to reduce pollutant gas emissions, to carry out repairs and renovations, to hire qualified professionals to do this;

6) To organize and send the information of the title certificate book (libre) of the vehicles equipped with technological device reducing the amount of pollutant gas emissions by identifying the quantity and type, electronically and manually every three months to the ministry or the delegated appropriate organ.

## 10. የተሽከርካሪ አስመጪ፣ ገጣጣሚ ወይም አምራች ድርጅት ወይም ግለሰብ ግዴታዎች

ማንኛውም የተሽከርካሪ አስመጪ፣ ገጣጣሚ ወይም አምራች ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚያስገባቸው ወይም የሚያመርታቸው ወይም

## 10. Obligations Vehicle importer, assembler or manufacturer enterprise or individual

Any vehicle importer, assembler or manufacturer of new or used vehicles imported or manufactured or fitted by an

የሚገጣጥማቸው አዲስ ወይም ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች፦

1) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠናቸው የሀገሪቱን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን ያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤
2) ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ልኬት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የማውጣት፤

ግዴታዎች አሉበት።

assembler or manufacturing company or individual shall have the following obligations:

1) Ensuring that their pollutant gas emissions meet the country's pollutant gas emissions standards;
2) To issue a certificate of emission measurement verification for each vehicles.

## ክፍል ሦስት

## በተለያዩ አካላት የሚፈፀሙ ተግባራት

## Part Three

## Activities performed by various bodies

### 11. በሚኒስቴሩ የሚፈፀሙ ተግባራት

በሚኒስቴሩ የሚፈፀሙ ተግባራት፦

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ከተሽከርካሪዎች የሚወጣውን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለሚያቀርቡ ድርጅቶች ወይም ለቴክኒክ ምርመራ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤
2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተቀመጡት መስፈርቶች ካልተሟሉ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጥያቄው በቀረበ

### 11. Activities to be performed by the Ministry

Activities to be performed by the Ministry:

1) By ensuring that the requirements set forth in Article 6 of this directive are met, it grants, renews, and cancels competency assurance license of companies that provide technological results to reduce the amount of polluting gas emissions from vehicles or technical inspection institutions.
2) If the requirements set forth in Article 6 of this directive are not met, a written response will be given to the applicant within five

አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ምላሽ ይሰጣል፤

3) ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተሽከርካሪዎችን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ እንዲወጣ ወይም እንዲሻሻል ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፣

4) ሁሉም በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ እና ድንገተኛ ምርመራ ሲያደርጉ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠናቸው በተቀመጠው ደረጃ መሠረት የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፤

5) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠናቸው ከተቀመጠው ደረጃ በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ስታንዳርዱን እንዲያሟሉ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

6) ወደ ሀገር የሚገቡ በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች የተቀመጠውን የበካይ ጋዝ ልቀት ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

7) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ከተሽከርካሪዎች የሚወጣውን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች እንዲገጥሙ ይከታተላል፤

working days after the request for a competency assurance license is submitted;

3) In cooperation with the stakeholders, it will raise or improve the emission level of vehicles, Monitors and verifies;

4) Ensures that all fuel-user vehicles perform annual and emergency inspections to ensure that their emission levels are up to standard;

5) It regulates vehicles whose emission level of pollutant gas exceeds the set level from import to the country;

6) Fuel-user vehicles entering to the country shall meet the set emission standards;

7) In coordination with the concerned bodies, it monitors the installation of technologies that can reduce the amount of polluting gas emitted from vehicles;

8) የተሽከርካሪዎችን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ አተገባበር በተመለከተ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

9) ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን መረጃዎችን ከዘርፉ ቴክኖሎጂ መሣሪያ አስመጪዎች፣ ለማሰራጨት ወይም ለመግጠም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከወሰዱ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ሪፖርት ይቀበላል፤ ያደራጃል፣ ይተነትናል ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፤

10) የተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቀነስ የሚረዱ አሰራሮች እና ቴክኖሎጂዎች እንዲለሙ ለማድረግ ጥናትና ምርምር የሚያካሂዱ አካላትን ይደግፋል፤ እውቅና ይሰጣል፤

11) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን መለኪያ መሣሪያዎች በየዓመቱ ብቃታቸው መረጋገጡን ወይም ካሊብሬት መደረጋቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

12) አስፈላጊ መሆኑን ሲያምን በተሽከርካሪዎች ላይ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ድንገተኛ ምርመራ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

13) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ የቴክኖሎጂ መሣሪያ የተገጠመላቸውን

8) Creates awareness regarding the implementation of vehicle emissions standards;

9) Collect, organizes, analyzes, and disseminates reports on emissions from vehicles by organizations or individuals who hold qualification licenses for the importation, distribution, or installation of technological equipment.

10) Supports and recognizes bodies that conduct research to develop systems and technologies that help to reduce vehicle emissions;

11) Follows and controls that pollutant gas emission measurement devices are verified or calibrated annually;

12) If it deems necessary, it conducts emergency inspection of the amount of pollutant gas emission on vehicles and takes corrective measures;

13) Receives reports from enterprises or individuals who

ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (ሊብሬ)፣ ብዛትና ዓይነት በመለየት መረጃዎችን በማደራጀት በኤሌክትሮኒክስ እና በማንዋል በየሦስት ወር ለሚኒስቴሩ ወይም ውክልና ለተሰጠው አግባብነት ያለው አካል ሪፖርት የመላክ፤

## 12. <u>አግባብነት ባለው አካል የሚፈፀሙ ተግባራት</u>

አግባብነት ባለው አካል ሚፈፀሙ ተግባራት፡-

1) በቢሮው የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ምርመራ ሲያደርጉ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠናቸው በተቀመጠው ደረጃ መሠረት ያስለኩና ሰርተፍኬት የያዙ መሆኑን ያረጋግጣል፤

2) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠናቸው ከተቀመጠው ደረጃ በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች እንዲያስተካክሉ ያደርጋል፤ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ በማያስተካክሉ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እምርምጃ ይወስዳል፤

3) ሁሉንምበነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ድንገተኛ የተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ምርመራ ያደርጋል፤ ማስተካከያ እንዲያደርጉ ያደርጋል፤ በማያስተካክሉ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

have obtained competency assurance license for distribution or installationof technological devices that measure the level of pollutant gas emissions and it captures data, analyzes, and gives it to researchers.

## 12. <u>**Activities to be performed by the appropriate organ**</u>

Activities to be performed by the appropriate organ:

1) During the annual inspection of vehicles registered by the office, it verifies that their emission levels of pollutant gas are measured according to the set standards and that they have a certificate;
2) It shall fix the vehicles whose emission level of pollutant gas exceeds the set level and take administrative measure against those who do not fix it within the given time;
3) Shall conduct an emergency emission inspection of all fuel-user vehicles, makes adjustments and takes administrative action against those who do not correct it;

4) የተሽከርካሪዎችን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን ይተገብራል፤ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

5) የበካይ ጋዝ ልቀት መለኪያ መሣሪያዎች በየዓመቱ ብቃታቸው መረጋገጡን ወይም ካሊብሬት መደረጋቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

6) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቀነስ በተሽከርካሪዎች ላይ የተገጠሙ ቴክኖሎጂዎች ውጤታማነትን በመከታተል ይቆጣጠራል፤

7) የተሽከርካሪዎችን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ አተገባበርን በተመለከተ ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ይፈጥራል፣ መረጃዎችን በማደራጀት ለሚኒስቴሩ እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1) ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገበ ተሽከርካሪ በወጣው ደረጃ መሠረት ተለክቶ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት መያዝ አለበት።

2) በምርመራ ወቅት የበካይ ጋዝ ልቀት

4) Shall implement, follow up and control vehicle greenhouse gas emission standards implementation;

5) Follow up and control that pollutant gas emission measurement devices are verified or calibrated annually

6) Follow up and controls the effectiveness of technologies installed on vehicles to reduce pollutant gas emissions;

7) Creates awareness among various organs regarding the implementation of vehicle emissions standards, organizes information and reports to the ministry and the concerned organ.

## Part four

## Miscellaneous provisions

### 13. Transitional Provisions

1) Within six months from the date of issuance of this directive, any vehicle registered in Ethiopia must be measured according to the issued standard and have a certificate of verification.

2) During inspection, a vehicle

መጠን ደረጃ ሳያሟላ የተገኘ ተሽከርካሪ ለምርመራ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ አስተካክሎ በማስለካት ሰርተፍኬት መያዝ አለበት፡፡

3) በምርመራ ወቅት የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ ሳያሟሉ ተገኝተው በተሰጣቸው የአራት ወራት ጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከያ በማድረግ አስለክቶ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ያልያዘ ተሽከርካሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 መሠረት የተቀመጠው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

found not to meet the level of emission of pollutant gas standard must have a certificate of correction within four months from the date of it was submitted for inspection.

3) During the inspection, the vehicle found not to meet the level of pollutant gas emission level standard and without making corrections within the given four-month time limit shall be subject to the administrative measures set forth in Article 16 of this directive.

## 14. <u>ክልከላዎች</u>

የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ለማንኛውም ሰው የተከለከለ ነው፡-

1) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃን በማሟላት ሰርተፍኬት ያልተሰጠው ተሽከርካሪ ይዞ በመንገድ ላይ ማሽከርከር፤
2) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለማስለካት ተሽከርካሪው ወደ ምርመራ ተቋም በሚቀርብበት ወቅት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (ሊብሬ) ይዞ አለመቅረብ፤
3) በኢትዮጵያ የወጣውን ደረጃ ያላሟላ የበካይ ጋዝ ልቀት መቀነሻ መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማምረት፣ ማሰራጨት፣

## 14. <u>Prohibitions</u>

Committing the following activities is prohibited for any person:

1) Driving on the road a vehicle that has not been certified certificate to meet the emissions standards;
2) Failure to bring the title certificate book(Libre) when the vehicle is brought to the testing institution to measure the amount of pollutant gas emissions;
3) Importing, producing, distributing, installing or using emission reduction devices that

መግጠም ወይም መጠቀም፤

4) ከተሽከርካሪ የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን መለኪያ መሣሪያን በወጣው ደረጃ መሠረት ገዝቶ በሥራ ላይ አለማዋል፤

5) የብቃት ማረጋገጫ ሳያወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ለመለካት ወይም የበካይ ጋዝ ልቀት መቀነሻ መሣሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማምረት ወይም ለመግጠም የንግድ ፈቃድ ማውጣት፤

6) የአዋጁን እና በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ማናቸውንም ድንጋጌዎች መተላለፍ፤

## 15. የሕግ ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ ግዴታ የተጣለበት ሰው የአዋጁን እና የመመሪያውን ድንጋጌዎች ተላልፎ ከተገኘ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## 16. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1) የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሌለው ተሽከርካሪ የአሽከርካሪው ባለቤት መረጃ ተይዞ የ15 ቀናት ጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያስተካክል የጽሁፍ

do not meet the standards issued by Ethiopia;

4) Failure to purchase and operate a vehicle exhaust gas emission measurement device according to the issued standards;

5) Issuing business license to measure pollutant gas emissions or import pollutant gas emission reduction device without issuing a competency assurance license for import, manufacture or install;

6) Violation of the proclamation and any provisions of this directive.

## 15. Legal Liability

Subject to the provision of liability under the relevant law, if the person who is obliged to comply with this directive is found to have violated the provisions of the proclamation and the directive, shall be subject to administrative measures provided under Article 16 of this directive.

## 16. Administrative measures

1) A vehicle without a certification of greenhouse gas emission levels shall prompt the issuance of a written warning to its owner, requiring them to

ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረበ ለአሥራ አምስት ተከታታይ ቀናት ከእንቅስቃሴ እንዲታገድ ተደርጎ የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

2) ከእንቅስቃሴ በታገደ እና የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉ አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ ማረጋገጫ ካላቀረበ ለሦስት ወራት ከእንቅስቃሴ ይታገዳል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች በቅደም ተከተል ተወስደውበት አስተካክሎ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ ተሽከርካሪው ከእንቅስቃሴ ይታገዳል፡፡

4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 (1)፣ (2)፣ (3) እና (5) ከተመለከቱት ክልከላዎች አንዱን የፈፀመ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡

5) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ከንዑስ አንቀጽ (4) እና (6) ከተመለከቱት ክልከላዎች አንዱን የፈፀመ

provide the necessary documentation and rectify the issue within a 15-day time limit. If the owner fails to comply within this time frame, the vehicle shall be suspended from operation for fifteen consecutive days, accompanied by a final written warning.

2) If the vehicle remains suspended and the owner fails to provide proof of greenhouse gas emission levels within 15 days following the final warning, the vehicle shall face suspension from operation for three months.

3) If the administrative measures outlined in sub-articles (1) and (2) are implemented, and the vehicle still fails to provide a certificate demonstrating compliance with greenhouse gas emission levels, the vehicle shall be permanently suspended from operation.

4) Any person who violates any of the prohibitions stated in Articles 14 (1), (2), (3), and (5) of this Directive shall be subject to the administrative measures described in sub-articles (1) to (3) of this Article, respectively.

ማንኛውም ድርጅት ወይም ግለሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

6) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ከንዑስ አንቀጽ (3)፣ (4) እና (5) ከተመለከቱት ክልከላዎች አንዱን ለሁለተኛ ጊዜ የፈፀመ ማንኛውም ድርጅትወይም ግለሰብ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ለሦስት ወራት ይታገዳል፡፡

7) ከላይ በንዑስ አንቀፅ 6 በተገለፀዉ የጊዜ ገደብ ካላስተካከለ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

## 17. ስለቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት

1) በመመሪያው መሠረት በተሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ቅሬታውን አገልግሎቱን ለሰጠው አካል ኃላፊ ቅሬታው በተፈጠረ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2) ቅሬታ የቀረበለት ኃላፊ ለቀረበው ቅሬታ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

3) ኃላፊው በሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ

5) Any organization or individual who violates the prohibitions specified in sub-articles (3), (4), and (6) of Article 14 of this Directive shall receive a final written warning if it is their first offense.

6) Any organization or individual who continues to violate the prohibitions mentioned in sub-articles (3), (4), and (5) of Article 14 of this Directive shall have their qualification license suspended for three months.

7) If the deadline specified in sub-article (6) is not adhered to, the qualification license shall be revoked.

## 17. Grievance submission and resolution system

1) Any person who has a complaint with the service provided according to the directive can submit the complaint in writing to the head of the department that provided the service within five working days of the complaint.

2) The officer to whom a complaint is submitted must respond in writing to the complaint within five working days.

ሰው ቅሬታውን በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለሚኒስትሩ ወይም አግባብነት ላለው አካልኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡

4) ሚኒስትሩ ወይም አግባብነት ያለው አካልኃላፊ ለቀረበው ቅሬታ በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5) ሚኒስትሩ ወይም አግባብነት ያለው አካልኃላፊ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## 18. የአገልግሎት ክፍያ

1) ማንኛውም ድርጅት ወይም ግለሰብ በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲወስድ እና ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች አገልግሎቶችን ሲጠይቅ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

2) ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ የሚሰጠው የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስተሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወስናል፡፡

## 19. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያበተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

3) A person who is dissatisfied with the officer's response can submit his complaint in writing to the minister or the officer of the appropriate organ within three working days.

4) The Minister or the officer of the appropriate organ shall issue a written administrative decision to the complaint within fifteen working days.

5) The decision of the Minister or officer of the appropriate organ shall be the final administrative decision.

## 18. Service Fee

1) Any enterprise or individual must pay a service fee when taking a competency assurance license and requesting other related services in accordance with this directive.

2) The Ministry shall establish the service fee prescribed by this directive through regulations issued by the Council of Ministers.

## 19. Inapplicable Laws

Any directive or customary practices that contradict with this directive shall not apply to matters covered by

20. **<u>ስለ አባሪ ሰነዶች</u>**

የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ያወጣው ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ እና ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙ አባሪ ሰነዶች የዚህ መመሪያ አካል ይሆናሉ፡፡

21. **<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

22. **<u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ድህረ-ገፅ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር)**
**የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**

this directive.

**20. <u>Attachment documents</u>**

The emission standard for vehicle emissions issued by the Ethiopian Standards Institute and the attached documents to this directive shall be part and parcel of this directive.

**21. <u>Amendment the Directive</u>**

The Ministry may amend the directive when it deems necessary.

**22. <u>Effective date of the Directive</u>**

This directive shall be registered with the Ministry of Justice and shall take effect from the date it is published on the Ministry's website

.

**Alemu Sime (Dr.)**
**The Minister of**
**Ministry of Transport and Logistics**

## አባሪ-1

# የአገልግሎት መጠየቂያ/ማመልከቻ ፎርም

1) የአመልካች ስም-----------------------------------------------------------------------------------------------------
2) የድርጅቱ/የአመልካቹ አድራሻ------------------------------------------------------------------------------------
3) የንግድ ስም (ካለ)--------------------------------------------------------------------------------------------------
4) የሥራ አስኪያጁ ስም---------------------------------------------------------------------------------------------
5) ለሥራው የተመደበ ካፒታል-------------------------------------------------------------------------------------
6) የሠራተኛ ብዛት---------------------------------------------------------------------------------------------------
7) የጠየቀው የአገልግሎት ዓይነት----------------------------------------------------------------------------------
8) የድርጅቱ ቢሮ እና የመሥሪያ ቦታ------------------------------------------------------------------------------
   ሀ) የግል ይዞታ------------------------------------------------------------------------------------------
   ለ) የኪራይ-----------------------------------------------------------------------------------------------
9) አመልካች ራሱ(ባለቤቱ) ከሆነ (ይህንኑ ይግለፁ)-----------------------------------------------------------
10) በውክልና ከተጠየቀ(ይህንኑ ይግለፁ) --------------------------------------------------------------------------
11) ያያዟቸው ሰነዶች ዝርዝር ፊት ለፊት ያለው ሳጥን ውስጥ √ምልክት (ቲክ) ያድርጉ?
    ሀ) የአመልካች የታደሰ የቀበሌ መታወቂያካርድ ኮፒ
    ለ) የአመልካች የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ኮፒ
    ሐ) የባለይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/የኪራይ ውል/ኮፒ
    መ) የውክልና ሥልጣን ማስረጃ ሰነድ ኮፒ
    ሠ) የተወካይ የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ኮፒ
12) እኔ አመልካች---------------------------------------------------ከላይ የተዘረዘሩት -----ገጽ ሰነዶች በእውነት የቀረቡ መሆናቸውን እየገለፅሁ በምወስደው የ-----------------------------------------------የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በትክክልና ያለምንም ማጭበርበር ለመሥራት ቃል የገባሁ መሆኔንና በእኔ ጥፋት ምክንያት ለሚመጣው ተጠያቂነት ሙሉ ኃላፊነት የምወስድ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ስም፡-----------------------------------------

ፊርማ፡-----------------------------------------

ቀን፡-----------------------------------------

**Anex -1**

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

## Service request/application form

1) Applicant's name------------------------------------------------------------

2) The applicant's address of the organization-------------------------------

3) Trade name (if any) ------------------------------------------------------------

4) Name of the manager----------------------------------------------------------

5) Capital allocated to the work------------------------------------------------

6) The number of workers-------------------------------------------------------

7) The type of service requested-----------------------------------------------

8) The company's office and workplace---------------------------------------

   a) Private possession-----------------------------------------------------

   b) Rent-----------------------------------------------------------------

9) If the applicant is the owner (I say the same) -----------------------------

10) If requested by proxy (specify the same) ----------------------------------

11) Put a √ mark (thick) in the box in front of the list of documents you have attached?

   a) Copy of applicant's renewed Kebele ID card----------------------------

   b) Copy of applicant's national identity card-------------------------------

   c) Owner's confirmation map of the lease agreement----------------------

   d) Copy of power of attorney document------------------------------------

   e) Copy of representative's ID card------------------------------------------

I, the applicant ……………… hereby declare that the documents listed on ………… page above are true and correct and that I undertake to execute the Certificate of Qualification of ………… accurately and without fraud and that I take full responsibility for any liability arising from my negligence.

applicant name ----------------------------------------

Signature ---------------------------------------------

Date ----------------------------------------------------

**አባሪ-2**

# <u>የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ደረጃ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት</u>

1. አገልግሎት የሰጠው ተቋም ስም:--------------------------------------------------------------------
2. የተቋሙ አድራሻ:-------------------------------------------------------------------------------
3. የአገልግሎቱ ዓይነት:---------------------------------------------------------------------------
4. የተሽከርካሪው ባለንብረት ስም:-------------------------------------------------------------------
5. የተሽከርካራ ባለንብረት አድራሻ:-----------------------------------------------------------------
6. የተሽከርካሪው ዓይነት:--------------------------------------------------------------------------

    ሀ) የመለያ ቁጥር ሠሌዳ:--------------------------------------------------------------------

    ለ) የሻንሲ ቁጥር -------------------------------------------------------------------------

    ሐ) የሞተር ቁጥር---------------------------------------------------------------------------

ንብረትነቱ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰው ተቋም/ግለሰብ የሆነውና ዓይነቱ ከላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ በተቋማችን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ልኬት ተደርጎለት ደረጃውን አሟልቶ ስለተገኘ ይህ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት ዛሬ ---/----/20--- ዓ.ም ከተቋማችን የተሰጠው መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

| የዕድሳት ዘመን | የዕድሳት ዘመን | የዕድሳት ዘመን | የዕድሳት ዘመን |
|---|---|---|---|
| ለ-------------ዓ.ም<br>ታድሷል<br>የኃላፊ ስም----------------<br>ፊርማ-----------------------<br>ቀን-------------------------<br><br>ክብ ማኅተም | ለ-------------ዓ.ም<br>ታድሷል<br>የኃላፊ ስም----------------<br>ፊርማ----------------------<br>ቀን-------------------------<br><br>ክብ ማኅተም | ለ-------------ዓ.ም<br>ታድሷል<br>የኃላፊ ስም---------------<br>ፊርማ---------------------<br>ቀን------------------------<br><br>ክብ ማኅተም | ለ-------------ዓ.ም<br>ታድሷል<br>የኃላፊ ስም----------------<br>ፊርማ----------------------<br>ቀን------------------------<br><br>ክብ ማኅተም |

**Anex -2**

# Emission level certification certificate

1. The name of the institution that provided the service------------------------
2. Address of the institution--------------------------------------------------------
3. Type of Service: ------------------------------------------------------------------
4. Name of the owner of the vehicle: ----------------------------------------------
5. Address of Vehicle Owner: -------------------------------------------------------
6. Type of Vehicle:-------------------------------------------------------------------

a) Plate No ---------------------------------------------------------------------

b) Chassis number----------------------------------------------------------------

c) Motor No ---------------------------------------------------------------------

We hereby certify that the vehicle, which is owned by the institution/individual mentioned in number 1 above and of the type indicated above, has been tested by our institution for its pollutant gas emissions and has been found to meet the standards. We hereby certify that this certificate of verification was issued by our institution on ..../.....202--

| Renewal | Renewal | Renewal | Renewal |
|---|---|---|---|
| Renewed for.......year<br>Name of the officer<br>Signature-------------<br>Date-------------------<br>Seal------------------- | Renewed for.......year<br>Name of the officer<br>Signature-------------<br>Date-------------------<br>Seal------------------- | Renewed for.......year<br>Name of the officer<br>Signature------------<br>Date------------------<br>Seal------------------- | Renewed for.......year<br>Name of the officer<br>Signature-------------<br>Date-------------------<br>Seal--------------------- |